የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፳፭
አዲስ አበባ–የካቲት ፳፬ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 25
ADDIS ABABA - 3rd March, 1998

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፻፩/፲፱፻፺ ዓ·ም
ከደቡብ አፍሪካ ሪፐብሊክ ጋር የተደረገ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ............. ገጽ ፮፻፺፯

CONTENTS

Proclamation No.101/1998
The Republic of South Africa Air Transport Service Agreement Ratification Proclamation ....... Page 697

### አዋጅ ቁጥር ፻፩/፲፱፻፺
### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በደቡብ አፍሪካ ሪፐብሊክ መካከል የተደረገውን የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በደቡብ አፍሪካ ሪፐብሊክ መካከል እ·ኤ·አ· ሜይ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፯ በኬፕ ታውን በመፈረሙ፣

ስምምነቱ በሥራ ላይ የሚውለው ተዋዋዮቹ ሀገሮች ፡ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መዋዋልና ተፈጻሚ ማድረግን በተመለከተ ፡ ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቶቻቸው መሟላታቸውን በዲፕሎማቲክ መስመሮች ከተገላለጹበት ዕለት ጀምሮ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተመለከተ በመሆኑ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የካቲት ፳፬ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፣

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### PROCLAMATION No. 101/1998
### A PROCLAMATION TO RATIFY THE AIR TRANSPORT SERVICE AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE REPUBLIC OF SOUTH AFRICA

WHEREAS, an Air Transport Service Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of South Africa, was signed in Cape Town, on the 14th Day of May, 1997;

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall come into force on the date on which the Contracting Parties have notified each other, through diplomatic channels, of the fulfilment of their constitutional formalities concerning the conclusion and implementation of international agreements;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 3rd day of March, 1998;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ከደቡብ አፍሪካ ሪፐብሊክ ጋር የተደረገ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፻፩/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በደቡብ አፍሪካ ሪፐብሊክ መካከል እ·ኤ·አ· ሜይ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፯ ኬፕታውን ላይ የተፈረመው የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ስምምነት ጸድቋል።

፫· <u>የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር ሥልጣን</u>

የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፳፬ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፳፬ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as "The Republic of South Africa Air Transport Service Agreement Ratification Proclamation No. 101/1998."

2. *Ratification of the Agreement*

The Air Transport Service Agreement signed in Cape Town on the 14th Day of May, 1997 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of South Africa is hereby ratified.

3. *Power of the Minister of Transport and Communications*

The Minister of Transport and Communications is hereby empowered to undertake all acts necessary for he implementation of the Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 3rd day of March, 1998.

Done at Addis Ababa, this 3rd day of March, 1998.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE